==========

ትምህርተ ደብተራ

ግንቦት
17/2012 e.c

==========

:::::::::::::::::: መግቢያ ::::::::::::::::::
ሰላም ኢትኤላውያን እንደምናችሁልን ይህንን ጥበብ እምንማረው አንድም ለራሳችን አንድም ለሰው ሁሉ አንድም ለሀገራችን ከሀገራችን ነውና የሀገርም ሀብት ነውና አደራ በተማራችሁት ትምህርት መልካሙን ሁሉ አስተምሩ አድርጉ ስማዝያስ ለአለም መጥፎ ነገር ቢያስተምርም ፈጣሪ በአንድም በሌላም ለወዳጆቹ አስማቱን ጥበቡን አስተምሮዋል ለኖህም ቢሆን መድሐኒት ይሆኑት ዘንድ 1500 የህክምና እፅዖች ተሰቶታል ለሰሎሞንም ቢሆን ጥበብን እንዲሁ ከ500 በላይ የጥበብ እና የመድሐኒት እፆች ተሰጥተውታል እነርሱን በዝርዝር እናያለን አደራ እናንተ ትልቅ ሀላፊነት አለባችሁ እና መጥፎውን ሳስተምር እናንተም መጥፎ እንደሆነ አውቃችሁ ተማሩ ለመማር ብቻ

ክፍል አንድ

::::::::::::::::::ምዕራፍ፡፩ ::::::::::::::::::::::
ለፀሎት(ለምስሀብ) አስፈላጊ ነገሮች

ምስሀብ ማለት ማቅረቢያ መሳቢያ ማለት ነው ::መናፍስትን መሳብ መጥራት ይቻላል ማየትም እንዲሁ አንዳንዱ በድምፅ ያወራሉ ያ አንሾካሿኪ ይባላል ለምሳሌ ስለአንድ ሰው ወይም ስለ ሌላ ነገር ማወቅ ስንፈልግ ጠርተን ከጀርባችን ሆኖ ይጠይቀናል የምንፈልገውን ከጠየቅን በኋላ ይልስልናል ከዛ በመሸኚያ እንሸኘዋለን ማለት ነው ምስሀብ ሁለት አይነት ነው
፩)ምስሀበ መላዕክት ወፃድቃን
፪)ምስሀበ ፀሊማን ዛር ወአጋንንት
ጂንያት ናቸው ::
ታዲያ ምንም ጊዜ ፀሎት ሁሉ ለማቅረብ ነው ወይ መንፈስ ቅዱስን ወይ ደሞ እርኩሳን መናፍስትን :: መልካም ታዲያ ፀሎት ሲደረግ ምን መደረግ አለበት ??

-ለሴት 12 ቀን ለወንድ 7 ቀን ከግብረ
ስጋ መቆጠብ
-ከጣፋጭ መቆጠብ ጨውም ጨምሮ
- የፀሎት ቦታ ያስፈልጋል ይህም በዚያ ቦታ ሁሌ
መላዕኩ ወይ መንፈሱ አንዴ በጀመራቹህበት
ሰዐት ይጠብቃችኋልና
-ጠረጴዛ
-ሻማዎች በተለያየ ከለር
-የፀሎት ልብስ(ነጭ)
-የተለየ መሰዊያ መቁረጫ
-እጣን ወዘተ ..... ያስፈልጋል ሌላው
ደፋር መሆን እግዚአብሔር ሁሉን ለሚፈልግ ሁሉ
ይደረግለታል አንኳኩ ይከፈትላችኋል እንዳለ ሁሉን
ብትመረምሩ ሁሉ ክፍት ነው ይህ ሚስጥራዊ
አለም ልክ እንደ አይን ነው ስንጨፍን እና ስንገልጥ
የተለየ እንደሚሆን ሁሉ ማለት ነው ህሊናችሁ
አንዴ ሲገለጥ ሁሉን መመልከት ትችላላችሁ .....

መናፍስትን ለማናገር ንቃተ ህሊና ወይም የመንፈስ ሀይል የምንለው ነው ይሄ በልምምድ የሚመጣ ሲሆን ሁለተኛውን አይናችንን መክፈት(ማብራት) ማለት ነው።ይህንን ጥበብ meditation ይሉታል ግን ከዛም በላይ ነው ።በተለያየ መንገድም ይገለጣል ወይም ይተገበራል

የመጀመሪያው እና የተለመደው በአፈ ህፃን የሚተገበረው ነው ለምሳሌ በስመ አብ በፋማ ...በምስሀብ እግዚአብሔር ወከሳቴ ብርሀናት ዘከሰትከ ሎቱ ለወልደ ነጓድጓድ ዮሐንስ በደሴተ ቆጵሮስ ማኅተመ ዘነጸረ በደሴተ ፍጥሞ ከማሁ አርእየኒ ወፈውኮ መልአከ ኅቤየ ወይቁም በቅድሜየ እንበለ ድንጋፄ

ወፍርሀት ወይትናበበኒ በኅድዓት
ወበየውዓት ወእኮ በመዓልት ሰማየ
ሰጢቀክሙ ምድረ ከፊተክሙ ከማሁ
አርእዩ ለዝ ካህን እገሌ .....እግዚአብሔር
ዘፈነውኮ ለዑራኤል መልአክ መንግለ
እዝራ ከመ ያለብዎ ነገረ ጥበባት
ወነገረ ሚስጥራት ከማሁ ይትፈነው
መልአከ አየር ጌዶር ጊዶር ጌዶር አንዶር
*3 አክዞር *3 አላዞር*3 አስኮናዞር
*3በድንጋገ ኤርሚያስ ሊቀ ዚአክሙ
ነጽር መንገሌየ በከመ ተርእዩ ለሄኖክ
በፈለገ ኮበር ይርክብ ንፃሬ ኅቡዓተ
ሚስጢር ከማሁ ይርክበኒ ንጻሬ ህቡዓት
ነገረ ወከሳቴ ሚስር ያሸመሸምት
ያሸለቲን ያተላቱን ላይሊላ ኃይሊላ
ቢስሚላ መርዴል ወላሕምዲላሂ ረቢ
ለዓለሚን ሠናይሂ ወመጅጅሂ ንዑ *3
ተስሀቡ ኩክሙ አጋንንት ከመ ትንግሩኒ
ነገረ ሠናየ ወእኩየ ለገብርክሙ
እገሌ....ወለዝ ህፃን ...
ይሄ አየረ ጴጥሮስ እና ሌሎችም
የሚሳቡበት በጣም ሀይል ያለው ነው

ገቢርም አለው ይሄ ጥበብ ተዋርሶ አለው የፈለጋችሁትን ያደርግላችኋል ግን ዉርሾ ካለሁ መጥፎ ነው አንድም ንስሀ የለው አንድም በየአመቱ ግበር እዚህ አትሂድ ይላል አስቸጋሪ ነው ይህንን ለፈለገ ግን በ inbox awrugn ....

:::: ሌላው::::
የመስታወት ጥበብ ነው ንቃተ ህሊናን ለመሰብሰብ የሚጠቀሙበት ነው ይሄ ጥበብ የዱሮ ጥበብ ነው ::
እንደዉም ኢትዮ አስማት face book channal lay አይቻለሁ በመስታወት እንዴት መንፈስ ማቅረብ እንደሚቻል ያስተምራሉ ይህንን በአብዛኛውን በአረብ ሀገር የሚጠቀሙበት ሲሆን

ለንቃተ ህሊና ወይም መንፈስ ለማየት ይጠቀሙበታል ጨረቃ ሙሉ ስትሆን መስታወቱን አውጥታችሁ ከዛም 9 ሲሆን አስገብታችሁ ለወሰነ ሰአት ሻማ አብርታችሁ ግንባራችሁን በመስታወቱ መመልከት ለ7ቀን ከዛም መንፈሱ በመስታወት ያናግራችዋል ይህሲሆን ብርሀን በፍፁም መስታወቱን ሊያገኘው አይገባም ይህ ሂደት ለብዙ ነገርም ይጠቅማል በተለይ ለመጠየቅ ለማወቅም ጭምር ግን ማዘዝ እና ይህን አድርግ ቢሉት አይሰራም

ሌላው በእንስሳት የሚገኝ ነው ጥበብ new ይሄ ጥበብ ለምሳሌ በጅብ ቅንድብ

በፀሀይ አድርቀው ደቁሰው ቢኳሉ መናፍስትን ያያሉ በተጨማሪ የውሻ እንባ ,የድመት ቅንድብ ወዘተ በእፅዋት ደሞ ድጋም አለው በእርሱ ተደግሞ ለምሳሌ አነ ችፍርግ ወዘተ ለነዚህ ምስሀብ ይሆናሉ ሌሎች ወፍ አንቁር ቀጥና እፀ ሳቤቅ ወዘተ ይሆናሉ

ሌላው እና የመጨረሻው ጠለሰማት ለንቃተ ህሊና ይሆናሉ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ አባቶች ሲጠቀሙበት የነበረ እጅግ ጥልቅ ሚስጥር ያለው ሲሆን በአንድ በሶስት እና በአራት በሰባት ይሳላል ።በአንድ ሲሳል የፈጣሪን ሀይል ስንስብ በሶስት ሲሆን የስላሴ የሶስትነቱ ልዩ ሀይል ስንስብ የአራቱ የኪሩቤል ገፃት ምሳሌ
ጠለሰም ማለት አምሳል ውክልና ማስዋብ ማለት ሲሆን የሰይጣንን ስራ በጣጥሶ ይህንን የሚገለባበጥ ሰይፍ የሚያሳልፍ ማለት ነው ። ይህ ነው

ረቂቅ ሚስጥሩ
ገፀ ሰብዕ,,,,,,,,,, መንፈስ
ገፀ አናብስት ..... አእምሮ
ገፀ ንስር ,,,,,,,,,, ንፋስ
ገፀ ላም,,,,,,,, ስጋ ተተኪ ናቸው ።
እንዴት በቀለም ይጣላል (ይሳላል)
🔱 የህይወት መንገድን የሚጠብቅ
የሚዘጋ በላም አምሳል ይወከላል ።
👉 የስጋ አካላችን ልቦናችን የተሰራበት
የአፈር ምልክት ነው ። ታዲያ በዚህ
መልካችንን ያፈራነውን ቁሳዊ ሀብቻችን
ይጠበቃል ። ይህንን ሰይፍ ለማለፍ
ደግሞ ስሜቶቻችንን መቆጣጠር ተገቢ
ነው ይህንንም በታላቅ ፆምና ስግደት
በተፀማሪ ጥልቅ ሀሳብ maditation
(በነገራችን ላይ ይህ ጥበብ ጥንታዊ
አባቶቻችን የጀመሩት ሲሆን ዛሬ ዛሬ እኛ
ጀመርነው የሚሉ በተለይ ቻይናውያን
የተኮረጀ መሆኑን ልብ በሉሉልኝ በሌላ
ጊዜ በሰፊው አቀርባለሁ) ናቸው ።
ለዚህም ጤናማ ፣ እውቀትና ፣ ፅናት
ያስፈልገዋል ።

ገፀ ንስር
እንደ ንፋስ ነፃነትን የተቸረው የነፍሳችን መገለጫ ሲሆን እስትንፋስ ላይ ያለው እንቅስቃሴአችን በሙሉ በዚህ ይመራል ይህንን ንስርነታችንን በእኛ ስር አድርገን ለመብረርና ከኪሩቤል ሰይፎች ለማለፍ ደግሞ በመልካም ተግባር ልምምድ መኖር ዋናው መንገድ ሲሆን በጥልቅ ተመስጦ ውስጥ ገብቶ እግዚአብሔርን ማሰብና ተስፋን ሰንቆ መጓዝ የዚህ የነፍሳችንን ጠለሰም ቅኔ መፍቻ ቁልፎች ናቸው ::

ገፀ አንበሳ
መደቡ የእሳት መገለጫ ሲሆን
በአዕምሮአዊ ሀይል ባዘሉ ቃላቶች
ይነለፃሉ ይህም የሀይልና የመነቃቂያ
ተፈጥሮ የሚገራው በጥልቅ ምርምርና
ትግስት ተመርቶ በፈሪሀ እግዚአብሔር
በመተናነስና በትህትና የሚገኝ ጥበብ
እነዚን ጥልቅ ምስሎች (symbols)
እናያቸዋለን ጊዜው ሲደርስ
በውነት ከላይ ያሉትን ካለፈ በኃላ
የሚያገኙት ድንቅ ጥበብ ነው ።በውሀና
በመንፈስም ይገለፃል የህያውነትና
የዘላለማዊነት መገለጫ ሲሆን እምነት
፣ ስለምግባር ፣ ትግስት ፣ ምህረት ፣
ፅድቅና ሁሉንም የመቀበል የፍቅር ደረጃ
ላይ ሲደረስ የሚገኝ ነው
ሲሆን 7የሰባቱ አምዳት ምሳሌ ናቸው